የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው
ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of Washington DC
and its surroundings.

ከኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት የተሰጠ መግለጫ

ጥር 26 2004 ዓ. ም

# “ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ የተመሰረተ ሀገረ ስብከት መሠረቱ የጸና ነው ”

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪካዊትና ሐዋርያዊት እንደ መሆኗ መጠን የተሰጣትን አደራ ጠብቃና አስጠብቃ ለትውልድ ለማስተላለፍ በየዘመኑ በቃላት የማይገጽ መስዋዕት በታማኝ ልጆቿ አማካኝነት ከፍላለች። በእነዚህ ጊዜያት አባቶቻችን የነበራቸው ሕብረት እንደብረት የጠነከረ ስለነበር ፤ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጠበቅ የነበራቸው ትጋትና ቁርጠኝነት ምሳሌነት የነበረው እራሳቸው ተከብረው ፤ ቤተ ክርስቲያንንም አስከብረው ፤ በመልካም ተግባራቸው ምሳሌ በመሆናቸው በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ እንደ አይን ብሌን ይታዩ ነበር ። ከሊቃውንት አባቶቻችን አንደበት ይሰማ የነበረው እንደ ማር የሚጣፍጥ ፤ ተሰምቶ የማይጠገብ ሕይወት ቃል ሊቅነታቸውንና ታማኝነታቸው በተግባር ከማሳየቱ በተጨማሪ የሃይማኖት አባት ወግና ማዕረግ ምን እንደሆነ በተግባር አሳይተውን አልፈዋል ። የቀደሙትን አባቶችን የምናውቃቸው ለእኔ ሳይሆን ለወገኔ ሲሉ፤ ለራሳቸው ሀብትና ንብረት ከማስቀመጥ ይልቅ ያላቸውን ለድሆች ሲመጸውቱ ፤ የከተማን ግርግር ከማድነቅ ይልቅ በገዳም ተወስነው በጸሎት ተጠምደው ፤ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጠበቅ ሲተጉ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ምሳሌ ሲሆኑ ነው ።

ዛሬም ቢሆን ሕዝበ ክርስቲያኑ የናፈቀው በትህትና የተሞላ፤ ከስሜታዊነት የራቀ አባት ፤ በበጎ ምግባር ምሳሌ የሚሆንና ቃሉና ተግባሩ አንድ የሆነ የተሰጠውን መንፈሳዊ አደራ የሚጠብቅና ለቤተ ክርስቲያን ታማኝ የሆነ አባት ነው ። የምእመናን ልቦና ወደ ቤተ እግዚአብሔር በተመለሰበት ፤ ቤተ ክርስቲያን ዘርፈ ብዙ ፈተና በከበባት በዚህ ጊዜ ፤ አባት ለልጆቹ ምሳሌ ይሆናል እንጂ ፈተና መሆን አይገባም ነበር ። የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት የገጠመው ችግር እና ፈተና የአባትና የልጅን ግንኙነት የሚጎዳ ልጆች ቤት አዘጋጅተው አባት ደግሞ ወደ ቤት ከመግባት በዳር መቆየት የመረጡ በመሆኑ ነው ። አሁን ለምንሰማው ችግር ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር በሰው ልቦና ያለውን ጨምር ያውቃልና ባለቤቱ ዳኝነት እንዲሰጥ በጸሎት መጠየቅ ከሁሉም ክርስቲያን የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው።

የቤተ ክርስቲያን እንድነት ይጠናከር ዘንድ ፤ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጠበቅና ማስጠበቅ ዓላማው አደርጎ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት እና የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ በቃለ ዓዋዲ መሰረትና በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በአብያተ ክርስቲያናት ሙሉ ተሳትፎ የተቋቋመው ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን በእውነትና በታማንነት ለቤተ ክርስቲያን ዓላማ ታማኝ ሆኖ በግልጽነትና በታማኝነት ሁሉ ነገር እንዲከናዎን ፤ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ሲሆን ሀገረ ስብከቱ አሁንም ለዚህ ዓላማ ወደ ኋላ ሳይል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነት ብቻ እንዲፈጸም ፤ በአባቶችና በልጆች መካከል የዓላማ አንድነት እንዲጠናከር ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር የሚደሰትበት ሥራ እንዲከናወን ፤ ሁልጊዜ ይተጋል ።

ስልክ/Telephone: 703-360-0105 www.eotcdc.org Email: office@eotcdc.org
አድራሻ/Address: 4210 Corcoran St. Alexandria, VA 22309 ወይም/or P.O. Box 77363 Washington, DC 20013-7363